# የአባልነት ቅጽ

ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ በመንግስትም ሆነ በግሉ ዘርፍ እንዲሁም በሌሎች ሕዝባዊ ድርጅቶች ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለበት አሰራር እንዲሰፍንና ሙስናም እንዲወገድ የሚሰራ ተቋም ነው፡፡

## የስነ-ምግባር መርሆዎች

- እርስ በራሳችንም ሆነ ከሌሎች ጋር የሚኖረን የሥራ ግንኙነት ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ሐቀኝነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡
- ማንኛውም ተግባራችንም ከጉቦ፣ ከሙስና እና አግባብ ከሌለው በስልጣን ወይም ባለን አብላጫ አቅም ከመጠቀም የተቆጠበ ይሆናል፡፡
- ማንኛውም ተግባራችንን ስንፈጽም ሕጋዊ፣ ሙያዊ ሰነ-ምግባርና ሰብአዊ ገደቦችን ማክበር ብቻ ሳይሆን ከኀብርተሰቡ አመኔታና ክብር የሚያገኝ ሊሆን ይገባል፡፡
- ማንኛውም ማኀበራዊ ሥራችን በዴሞክራስያዊ መርህ ላይ የተመሠረተ ሆኖ በተለይም ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያን ወክለን የምንወስደው እርምጃ የፖለቲካም ሆነ የተለየ እምነት ወገናዊ ሊሆን አይገባም፡፡
- በማንኛውም ቦታና ጊዜ ጉቦን፣ ሙስናን እና በስልጣን መባለግን በግልጽ ስናይ በትጋትና በመንፈስ ቆራጥነት መቃወም አለብን፡፡
- ጉቦን፣ ሙስናን እና በስልጣን መባለግን መቃወምና ማጋለጥ የምንችለው በተጨባጭ ጥናታዊ መረጃ ላይ በመደገፍ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር የትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ አመራር አካላት በሚያደርጉት ጥሪት ሁሉ አባላት የመሳተፍ መብትም ግዴታም አለባቸው፡፡
- ለትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ አመራር አካል የምትወዳደር/ የሚወዳደር እጩ በጊዜው ያላት/ያለው የፖለቲካም ሆነ ማንኛውም አቋም ከማኀበሩ አላማ ጋር የማይፃረር መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባት/አለበት፡፡

## እሴቶቻችን

- ፍትህ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ሰብአዊነት፣ ተአማኒነት፣ ተቆርቋሪነትና ዴሞክራሲ

## ራዕያችን

- በአገራችን ከሚገኙ ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በመተባበር በአህጉራችንና በአለማችን ያለው የፖለቲካና የመስተዳድር ገጽታ፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እና ማኀበራዊ ኑሮ፣ ከጉቦ ከሙስና እና በስልጣን ከመባለግ የፀዱ እንዲሆኑ ነው፡፡

**አላማችን**

1. ዜጐች ሕገመንግስቱ ያጐናፀፋቸውን መብቶችንና ግዴታዎችን ጠንቅቀው እንዲረዱና እንዲጠቀሙ ማሳወቅ፣
2. ኀብረተሰቡ ከሙስና ነፃ የሆነ የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጣ የሚያስችለው ባህል መፍጥር፣
3. የግልጽነትና የተጠያቂነት ባህል በመንግስት ሀላፊዎችና ማኀበረሰባዊ ተቋማት መሪዎች ዘንድ እንዲሰርፅ ሙሉ ጥረት ማድረግ፡፡

**የአባልነት መስፈርት**

- ማንኛውም ርዕቱ አመለካከት ያለው ግለሰብ የትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ አባል መሆን ይችላል፡፡

**ሀ. መደበኛ አባል**

ማለት ለአካለ መጠን የደረሰ በአንድ በተለየ የሙያ ዘርፍ በመስራት ልምድ ያካበተና በማህበሩ ህልውና ላይ ከፍተኛ ሚና የሚኖረው የፀረ-ሙስና ትግሉን የሚያግዝ ለመ/ቤቱ ህልውና ብሎም እድገት የበኩሉን ድርሻ ማበርከት የሚችል እንደሆነ በቦርዱ ግብዣ የተደረገለትና አመኔታ ያገኘ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው ያፀደቀለት ግለሰብ ነው፡፡ ይህ አባል የማኀበሩን የመተዳደሪያ ደንብና የማህበሩን ቃል ኪዳን የተቀበለ፣ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ እንዲሁም መደበኛ የአባልነት መዋጮን የከፈለ ሆኖ ሊመዘገብ ይችላል፡፡

**ለ. ተባባሪ አባል**

ማለት ማህበሩ የሚያካሄደውን የፀረ-ሙስና ትግል በሞራል፣ በሙያ፣ በገንዘብና በተለያዩ ቁሳቁሶች በመደገፍ የተሰለፈ ነው፡፡ ማንኛውም የማኀበሩን ዓላማ የተቀበለ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ ግለሰብ ተባባሪ አባል መሆን ይችላል፡፡

**ሐ. የክብር አባል**

ማለት በማኀበሩ ቦርዱ ቀርቦና በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀ በሙያውና በምግባሩ ለፀረ-ሙስና ትግል አርአያ መሆን የሚችል ግለሰብ የማህበሩ የክብር አባል ይባላል፡፡ ማንኛውም በሕብረተሰቡ ውስጥ ታዋቂነት፣ ተደማጭነት ያለው፣ በስነ- ምግባሩ የታወቀ ሙስናን ለመዋጋት ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ከማንኛውም የጥቅም ግጭት ነፃ የሆነ ግለሰብ የክብር አባል ሊሆን ይችላል፡፡

የአባልነት ክፍያ መዋጮ

- መደበኛ አባል ምዝገባ፡- 50 ብር በዓመት 50.00 / ሀምሳ ብር/
- የግለሰብ ተባባሪ አባል፡- መመዝገቢያና ዓመታዊ መዋጮ በቦርድ ይወሰናል

- የክብር አባል ለመመዝገቢያ፡- 500.00 /አምስት መቶ/ ብር በዓመት 100.00/አንድ መቶ/ ብር ነው፡፡

ከዚህ ቅጽ/ ፎርም ጋር የተካተተውን የትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ አባላት የስነ-ምግባር መርሆች፣ እሴቶች፣ ራዕይ እና አላማዎች በጽሞና አንብቤ ተረድቻለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ሀገሬን ዓለም ከደረሰበት የእድገት ደረጃ እንድትደርስ ከሙስና ከምዝበራ፣ ከዋልጌነት፣ የፀዳ በስነ-ምግባርና በጨዋነት የታነፀ ሕዝባዊና መንግስታዊ አስተዳደርና አሰራር እንዲሰፍን በሕዝቡም ዘንድ እንደባህል ተቆጥሮ እንዲዳብር ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤ ይህንን በመገንዘብ አቅሜ በፈቀደ ሁሉ ጊዜዬንም እውቀቴንም መስዋዕት በማድረግ ሙስናና ምዝበራ አድሎአዊነት እንዲወገድ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሰራርና አመራር እንዲጎለብት ሕዝብን በማስተማርና በማሳወቅ የአገርና የእድገት ጠንቅ የሆኑ አሰራሮች እንዲከስሙ በማሳሰብ ለዚህም በሙሉ ቁርጠኝነት ለመስራት የትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ አባል በሙሉ ፈቃዴ ለመሆን ይህንን የአባልነት መጠየቂያ ቅጽ ሞልቼ ስፈርም የተጠቀሱትን የስነ-ምግባር መርሆች እንዲሁም የማኅበሩን እሴቶችና ራእይ ለማክበርና ለመጠበቅ ቃለ በመግባት ነው፡፡

ስም ከነአያት ______________________________

መሥሪያ ቤት ______________________________

የሥራ ድርሻ ______________________________

(አድራሻ) ______________________________

ስልክ ቁጥር የሥራ ____________ የቤት ____________

ኢ-ሜይል ____________ ሞባይል ____________

መደበኛ አባል ____________

ተባባሪ አባል ____________

የክብር አባል ____________

በጥሬ ገንዘብ ____________ በቼክ ____________

**ፊርማ** ____________ **ቀን** ____________

ይህን ፎርም ከሞሉ በኋላ በሚከተለው አድራሻ ይላኩልን

**ትራንስፓረንሲ ኢትዮጵያ**
ብሔራዊ ስቴዲዮም አጠገብ፣ ከቀድሞ ኤርትራ ኤምባሲ ጐን፣
ጌታሁን ብርቄ ሕንፃ
ፖ.ሣ.ቁ 27847/1000
ስልክ፡ 251-11-5510738/6555508
ኢ-ሜይል tirat.ti@ethionet.et
www.transparencyethiopia.org
አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ